ማርች /21 1994

ስለጂሚ ካርተር የማርች 18 ደብዳቤ

1ኛ/ ያለው ሁኔታ እኔ እንደሚታየኝ ከሁሉ አስቀድመን ከዚህ ደብዳቤ ማየትና ማጉላት
ያለብን አቶ መለስ ዜናዊ ለመደራደር ፈቃደኛ አለመሆኑን ነው:: አልደራደርም ያለውም
የኛን ሃሳብና የኛን አጀንዳ ነጥቦች ገልጸን ሳይሆን "በማርች 14 ባቀረብኩት የመን
ደርደሪያ ሃሳብ በመመርኩዘ ድርድር እንደማይፈልግ አስታውቆኛል::" ነው የሚሉት ጂሚ
ካርተር:: በዚህ ሃሳብ ላይ እና ገና መልስ አልሰጠናቸውም ነበር:: አማራጭ ምክር
ቤቱና መድህን መልስ ሰጥተው እንደሆነ፣ ምንስ እንደመለሱ አላውቅም:: አቶ መለስ ለ
ድርድር አይቀርብም ያለውን ሌላ የሽግግር መንግሥት መቋቋም ጉዳይ እንደኛው እነሱም
እንደሚገፉበት ግን ለመገመት ይቻላል:: አትላንታ ላይ በዚህ ጥያቄ ላይ የጋራ ስምም
ነት /እና መኢሶኖች እስከዚህ ባናምንበትም/ ተደርሶ ነበርና:: የሆነ ሆኖ ጂሚ ካር
ተር "ባቀረብኩት የማርች 14 ፕሮፓዛል መሠረት አቶ መለስ አልደራደርም ብሏል" ብለ
ው የሚወነጅሉትና ለሙከራቸው ውድቀት በጽሁፍ ተጠያቂ የሚያደርጉት እሱን ነው::ይኸ
መቼስ በደንብ መሰመር ያለበት ጥያቄ ነው::
2ኛ/ አቶ መለስ ለመንደርደሪያ ሃሳብ መነሻ እንኳን አድርጌ አልቀበለውም የሚለው የ
ማርች 14ቱ ደብዳቤ የሚያቀርባቸው አራት ነጥቦች ምንድን ናቸው? 1ኛ/ የመጀመሪያው
ነጥብ ፕሮፓዛልም አይደለም:: ሁሉም በቅን መንፈስ ለመወያየትና ከነዚህ ውይይቶች የ
ሚሰተፈው አንዳች የፕሮፓጋንዳ ድል ላለመሻት ዝግጁ እንደሆነ ያላቸውን እምነት ይገል
ጻሉ:: አቶ መለስ በዚህ ነጥብ ምን ተቃውሞ እንደሚኖረው አይገባኝም:: 2ኛ/ሁሉም
ወገኖች አመጽን ትተው ለችግሮቻቸው ሰላማዊ መፍትሄ ይሻሉ ብዬ እገምታለሁ ይላሉ::ይ
ህም አቋም መግለጽ እንጂ ፕሮፓዛል አይደለም:: በእኛም በኩል በሰላማዊ መንገድ ለመ
ታገል ዝግጁነታችንን ገልጸናል:: አቶ መለስም ጂሚ ካርተር ፌብርዋሪ 14 በጻፉለን
ደብዳቤ እንዳሉት ከሆነ እንዲያውም አመጽን ካልተውም ጋር ለመወያየት ዝግጁ ነኝ ብሎ
ነበር:: አሁን ውይይት አሻፈረኝ ብሉ የሰጠው ሰበብ ይህንን አቋሙን የሚጻረር ይመስ
ላል:: ግን እስከዚህም አዲስ ነገር የለውም:: ፌብርዋሪ 14ቱ ደብዳቤ ላይም ቢሆን
" አመጽን ሪናውንስ ካላደረጉም ጋር ቢሆን..."ይላል እንጂ ወዲያው አከታትሎ "በ
ሰላም በፓለቲካው ሂደት ውስጥ ለመሳተፍ ያላቸውን ፍላጎት በጽሁፍ እስከገለጹ ድረስ"
ይላል:: አሁን ተመልሶ "በይፋ አመጽን ተተናል ካላሉ" ይላል:: የሆነ ሆኖ ጂሚ ካ
ርተር በግልጽ ያስቀመጡት ሁሉም ወገኖች አመጽን ለመተው ዝግጁ ናቸው ብለው እንደሚያ
ምኑ ነው:: መለስ በርግጥ ለሃገሪቱ ችግሮች በድርድር መፍትሄ የሚሻ ቢሆን ኖሮ ይህ
ም ነጥብ "በቃኝ ከነሱ ጋር አልወያይም" ለማለት የሚያበቃው ይዘት የለውም::

ችግርና ልዩነት ሊኖር የሚችለው በጂሚ ካርተር ፕሮፓዛል ነጥብ 4 እና 3 ላ
ይ ነው:: 3ኛው ነጥብ የሚለው ሁሉም ወገኖች እንዴት በአንድነት በፖለቲካው ሂደት
ተሳትፈው ለሃገሪቱ አንድ ቋሚ ህገመንግሥት የሚነድፉበትና በዚህ አማካኝነት ደግሞ ብ
ሄራዊና ክልላዊ ምርጫዎች እንዴት እንደሚካሄዱ መወያየት ነው ይላል:: እንዲያውም ይህ
የውይይቶቹ መአከላዊ ነጥብ ነው ይላል:: የነመለስን የቀየ አቋም እንጂ የኛን የሌላ
ሽግግር መንግሥት ጥያቄ አጀንዳው ውስጥ በቀጥታና ግልጽ በሆነ መንገድ አላስገባውም::
ይህንን የመሰለውን ጥያቄ "በጋራ ስምምነት" ማንሳት ይቻላል ከሚላቸው ሌሎች ጥያቄዎ
ች ውስጥ ያስገባው ይመስለናል:: የሆነ ሆኖ ይህ የማወያየት ሙከራው "እናንተም ሌላ
መንግሥት ካልተቋቋመ ብላችሁ እነአቶ መለስ ደግሞ ይህ ለድርድር አይቀርብም ስላሉ ው
ድቅ ሆነ አላለም:: እንግዲህ እነአቶ መለስ መጋለጥ ያለባቸው በነዚህ ጂሚ ካርተር
የውይይቶቹ መአከላዊ ነጥቦች በሚሏቸው ላይ ከኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ጋር መደ
ራደር የማይችሉ ኃይሎች በመሆናቸው ይመስለናል:: 4ኛው ነጥብ እንዲያውም ይህንን ሃ

